በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
TRANSPORT BUREAU

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖት ቢሮ

# የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት መሰረተ ልማት አስተዳደር

# መመሪያ ቁጥር 131/2014

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖት ቢሮ
# የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት መሰረተ ልማት አስተዳደር
# መመሪያ ቁጥር 131/2014

ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የወጣባቸው የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን የሚለሙበትና የሚተዳደሩበት መመሪያ የሌለው በመሆኑ በሀብቶቹ ላይ በርካታ ችግሮች ማለትም ስርቆት፣ በተሽከርካሪ ግጭት ምክንያት በመሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን፣ በግለሰብና በመንግስት ተቋማት የሚቀርቡ የይነሳልን ቅሬታዎችን ለመፍታት፣ የአገልግሎት ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል፣ የጥገና አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት፤

የተገነቡና እና በቀጣይ የሚገነቡ የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ደህንታቸው የተጠበቀ፣ ንጽህ፣ ምቹና ዘላቂ ሆነው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤

ከፍተኛ የመንግስት ወጪ ወጥቶባቸው የተገነቡና በቀጣይ የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች የአገልግሎት ዘመናቸውን ለማሳደግ፣ የግንባታና የጥገና ወጪዎችን ለመቀነስ፣ ሀብቶችን በላቀ ደረጃ ለማስተዳደር፣ የህብረተሰቡን የእርካታ ደረጃ ለማሳደግ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ለማጠንከር፣ የሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ ወጥ የሆነ የአጠቃቀምና የአስተዳደር ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ዓ.ም አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ደንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት መሰረተ ልማት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 131/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

2/ **“ባለድርሻ አካላት”** ማለት የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከትራንስፖርት ቢሮ ጋር በቅንጅት የሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ናቸው፤

3/ **"መጠለያ"** ማለት በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መስመሮች መነሻ፣ መተላለፊ እና መድረሻ ቦታ ያለው ሆኖ አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ከዝናብና ከፀሀይ የሚጠለሉበት የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ነው፤

4/ **"ተርሚናል"** በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት የህዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎችን እና ጭነቶችን ለመጫንና ለማውረድ እንዲውሉ የተገነቡ እና በቀጣይም የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች ናቸው፤

5/ **"ጊዜያዊ ተርሚናል"** በተለምዶ የህዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎችን ለመጫንና ለማውረድ በቢሮው አገልግሎት እንዲሰጡ የተለዩ ጊዜያዊ ቦታዎች ናቸው፤

6/ **"የማስታወቂያ አገልግሎት"** ማለት ከትራንስፖርት ቢሮ ጋር ውል በመግባት በመጠለያው አካል ላይ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ሰሌዳ እና በተርሚናል ውስጥ የሚገኙ ውስን ቦታዎችን በመጠቀም ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቅ ተግባር ነው፤

7/ **"አገልግሎት ሰጪ"** ማለት የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤

8/ **"የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት በከተማው ክልል ውስጥ 70 እና ከዚያ በላይ ተሳፋሪን የመጫን አቅም ያላቸው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን ነው፤

9/ **"የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት በከተማው ውስጥ በሚገነቡ የከተማ ጭነት ተርሚናል ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ናቸው፤

10/**"ሶስተኛ ወገን"** ማለት በትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ባለስልጣን በውል የሚተላለፍለት አካል ነው፤

11/**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በሚያስተዳድራቸው መሰረተ ልማቶች ማለትም የህዝብና የጭነት ተርሚናሎች፣ መጠለያዎች ወይም ፌርማታዎች እና ጊዜያዊ ህዝብ ትራንስፖርት ተርሚናሎች አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የትራንስፖርት መሰረተ ልማት መስፈርት

### 4. የህዝብ ትራንስፖርት መጠበቂያ መጠለያዎች ወይም ፌርማታዎች

የህዝብ ትራንስፖርት መጠበቂያ መጠለያዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡-

1/ በዋና መንገድ አካል በሚገኝ የእግረኛ መንገድ ላይ ሆኖ ለህዝብ ትራንስፖርት መሳፈሪያ እና መውረጃ አገልግሎት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፤

2/ ማንኛውንም እግረኛና ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎችን እንቅስቃሴ በማያውክ ቦታ ላይ የሚገነባ ሆኖ ከዋናው መንገድ ጠርዝ ቢያንስ በአንድ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝና የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

3/ በቀንና በማታ የሚታይ እና ተጠቃሚዎችን ከፀሀይ እና ከዝናብ መከላከል የሚያስችል መሆን አለበት፣

4/ የተጠቃሚዎችን እይታ ከማያስተጓጉል ቁስ የሚገነባ ሆኖ አደጋን መቋቋም የሚችል፣ ለጥገናና ለጽዳት አመቺ የሆነ፣

5/ የአገልግሎት መረጃ መስጫ ሰሌዳ ያለው፣

6/ የመጠለያው የጣሪያ ጎን ቢያንስ 1.8 ሜትር ፤ ከመሬት ያለው ከፍታ ደግሞ ቢያንስ 2.5 ሜትር እና ወርዱ 6 ሜትር መሆን አለበት፣

7/ ከአደባባይ እና ከመስቀለኛ መንገዶች ቢያንስ በ80 ሜትር እና ከግለሰቦችና ከድርጅቶች መግቢያና መውጫ በር 12 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ፣

8/ በአንድ መስመር ላይ በሚገኙ በሁለት መጠለያዎች መካከል ቢያንስ ከ300-500 ሜትር ርቀት ሊኖር ይገባል፣

9/ ከፍሳሽ ማስወገጃ ቦይዎች ቢያንስ ከ5-6 ሜትር ርቀት ላይ መገንባት፣

10/የትራንስፖርት የጉዞ ፍላጎት እና የህዝብ መገልገያ ማዕከላት ባሉባቸው ቦታዎች ላይ መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

### 5. የህዝብ ትራንስፖርት መናኻሪያዎች ወይም ተርሚናሎች

የህዝብ ትራንስፖርት መናኻሪያዎች ወይም ተርሚናሎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡-

1/ በከተማዋ በሚዘጋጅ አህዳዊ ፕላን ላይ በሚመላከቱ ክፍት ቦታዎች ላይ ይገነባሉ፣

2/ የተጠቃሚዎችን ደህንነት ለአደጋ የማያጋልጥ፣ ማንኛውንም የትራፊክ እንቅስቃሴዎች የማያውክ፣ ተሳፋሪን ለመጫን እና ለማውረድ ምቹ የሆነ፣ ከተለያዩ የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶች ጋር ተመጋጋቢ የሆነ እና የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ፣

3/ በቀንም ሆነ በማታ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል፣

4/ ከባቢያዊ ተስማሚነት ያለው፣ ከተለያዩ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማለትም ከሆስፒታሎች፣ ከትምህርት ቤቶች እና ከእምነት ተቋማት ወዘተ... ቢያንስ 180 ሜትር እንዲሁም ከመኖሪያ መንደር ቢያንስ 30 ሜትር ርቀት ሊኖረው ይገባል፣

5/ የአገልግሎት መረጃ መስጫ ስርዓት ያለው፣

6/ የተርሚናሉ  መግቢያናመውጫ ከአደባባይ እና ከመስቀለኛ መንገዶች ቢያንስ 80 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ፣

7/ የትራንስፖርት የጉዞ ፍላጎት እና የህዝብ መገልገያ ማዕከላት ባሉባቸው ቦታዎች ላይ መገንባት፣

8/ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማለትም እንደ መብራት፣ ውሃ፣ መጸዳጃ ቤት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ፣ የአገልግሎት ክፍያ ማከናወኛ ቦታ እና ለአረንጓዴ ልማት የሚውሉ ቦታዎችን ማካተት፣

9/ የተርሚናል አቀማመጥ ኬሚካላዊ ይዘትነት ካላቸው ፋብሪካዎች መራቅ ይኖርበቸዋል፡፡

## 6. <u>የጭነት ትራንስፖርት መናኻሪያዎች</u>

የጭነት ትራንስፖርት መናኻሪያዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡-

1/ በከተማው በሚዘጋጅ አህዳዊ ፕላን ላይ በሚመላከቱ ክፍት ቦታዎች ላይ የተገነባ፣

2/ የተጠቃሚዎችና የአገልግሎት ሰጪዎችን ደህንነት አደጋ ላይ የማይጥል፣ ማንኛውንም የትራፊክ እንቅስቃሴዎችን የማያውክ፣ ጭነቶች ለመጫን እና ለማራገፍ የሚያስችል እንዲሁም ጭነቶችን ለማሰራጨትና ለማስተላለፍ ምቹ የሆነ፣

3/ በተርሚናል ውስጥ ጊዜያዊ የጭነት ማስቀመጫ ቦታዎች የጭነቶችን  ባህሪዎች ባማከለ መልኩ መኖር ይኖርበታል፣

4/ ግልጽ ብርሃን ያለውና በቀንም ሆነ በማታ ምቹ በሆነ ሁኔታ መጠቀም የሚያስችል፣

5/ ለተጠቃሚዎች የአገልግሎት መረጃ መስጫ ስርዓት ያለው መሆን ይኖርበታል፣

6/ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም መብራት፣ ዉሃ፣ መጸዳጃ፣ የተጠቃሚዎች ማረፊያ፣ የአገልግሎት ክፍያ ማከናወኛ ቦታ፣የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ያለው ፤

7/ የተርሚናል አቀማመጥ ኬሚካላዊ ይዘትነት ካላቸው ፋብሪካዎች 180 ሜትር መራቅይኖርበታል፣

8/ ቀላል የሆኑ ጥገናዎች ሊከናወንባቸው የሚችሉ ቦታዎች ያላቸው፣

9/ ከባድ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ሊያስተናግዱ የሚችል አቅም ያላቸው፣

10/ የተለያዩ የጭነት ማንቀሳቀሻ ማሽኖች ሊይዝ የሚችል ስፍራዎች ያላቸው፣

11/ ድንገተኛ የሆኑ አደጋዎችን መቆጣጠር የሚያስችሉ ግብዓቶች ወይም የደህንነት መሳሪያዎች ያለው፣

12/ ለጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት ምልክቶችንና ማመልከቻዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 7. <u>ጊዜያዊ ተርሚናሎች</u>

ጊዜያዊ ተርሚናሎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡-

1/ በተቋሙ የተለየና ተቀባይነት ያገኘ እንዲሁም በቅርብ ርቀት አገልግሎት የሚሰጥ ሌላ ተርሚናል የሌለ መሆኑ የተረጋገጠ፣

2/ ለመሳፈርና ለመውረድ ምቹ የሆነ እና የትራንስፖርት ተጠቀሚዎችን ደህንነት እና ጤና ስጋት ላይ የማይጥል፣

3/ በቀንም ሆነ በማታ አገልግሎቱን ለመስጠት ምቹ የሆነ፣

4/ በትራፊክ ፍሰት እና በሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ጫና የማያሳድር፣

5/ ከተለያዩ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማለትም በሆስፒታሎች፣ በትምህርት ቤቶች እና በእምነት ተቋማት ላይ አሉታዊ ጫና የማያሳድር፣

6/ ሁለትና ከዚያ በላይ የመንገድ መስመር ያሉባቸው ቦታዎች ላይ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡

# <u>ክፍል ሦስት</u>

# <u>አገልግሎት ሰጪዎች እና ተጠቃሚዎች በመሰረተ ልማት አጠቃቀም ላይ የሚኖራቸው መብትና ግዴታ</u>

## 8. <u>የአገልግሎት ሰጪዎች ግዴታ</u>

1/ የህዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገና የተጠቃሚውን ደህንነት ያገናዘበ በትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ሰዓት መሰረት አገልግሎት መስጠት፣

2/ ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመደበ ቦታ ላይ ተሳፋሪን የማሳፈርና የማራገፍ፣

3/ ማናቸውንም እጥበትና ጥገና ማከናወን እና ከተሽከርካሪ የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በተርሚናል ውስጥ መጣል የለበትም፣

4/ የቴክኒክ ችግር ያለባቸውን ተሽከርካሪዎች ይዞ ያለመግባትና ያለማቆም፣

5/ ተርሚናሉ በሚያወጣው የአገልግሎት ህግና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት መስጠት፣

6/ ለተርሚናል አጠቃቀም የሚወጡ አሰራሮች ማክበርና መፈፀም፣

7/ ማንኛውም የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር ንፅህና እና ደህንነቱ የተጠበቀ ተሸከርካሪ ለአገልግሎት ማቅረብ፣

8/ በተርሚናል ውስጥ የሚገኙ መገልገያ ንብረቶችና ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም አለበት፡፡

## 9. <u>የህዝብ እና ጭነት ትራንስፖርት ተጠቃሚ</u>

1/ በተርሚናሉ ውስጥ በሚሰጡ የትራንስፖርት ስምሪት መሰረት አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፣

2/ በተርሚናል ውስጥ የሚገኙ መገልገያ ንብረቶችና ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፣

3/ ቆሻሻዎችን በተቀመጡና በሚዘጋጁ ማጠራቀሚያ መጣል ይኖርበታል፣

4/ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለስምሪት መስመሩ በተዘጋጀ ስፍራዎች ብቻ መጠበቅና አገልግሎት ማግኘት ይኖርበታል፣

5/ የህብረተሰቡንና የተርሚናሉን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ተቀጣጣይና መርዛማ የሆኑ ቁሶችን ይዞ መግባት የለበትም፣

6/ የህብረተሰቡን ምቾት የሚነሱ እንደ ቂቤ፣ በርበሬና የመሳሰሉትን ቁሶች በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፣

7/ ህብረተሰቡ በተርሚናል የሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎት በአግባቡና ተራን ጠብቆ አገልግሎት ማግኘት ይኖርበታል፣

8/ ህብረተሰቡ ለትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ ማንኛውንም ጉዳቶች በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አራት
# ተግባርና ኃላፊነት

## 10. የትራንስፖርት ቢሮ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ዓ.ም የተሰጡት ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቁ ሆነው ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ቢሮው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ ለመጠለያ መገንቢያ የሚሆኑ ቦታዎችን በጥናት ይለያል፤

2/ በማስተር ፕላኑ መሰረት ለትራንስፖርት ተርሚናል የተለዩት ቦታዎችን ይረከባል፤

3/ ለህዝብ እና ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲውሉ ጥያቄ የሚቀርብባቸውን ጊዜያዊ ተርሚናሎች የሚያገለግሉ ቦታዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አስፈላጊነታቸውን ይመረምራል፣ እውቅና ይሰጣል፣ መለያዎችን ያስቀምጣል፤

4/ ለመጠለያ እና ለተርሚናል ግንባታ የሚያገለግል ዲዛይን ያዘጋጃል፣፤

5/ ተርሚናል አጠቃቀምና የመጠለያ ጽዳት አገልግሎት መስጫ የስራ ሰዓትን ይወስናል፤

6/ ጥገና ለሚያከናውኑ አካላት ወይም ለሶስተኛ ወገን በጨረታ ውል ይሰጣል፣ ክፍያ ይፈጽማል፤

7/ መሰረተ ልማቶች የሚሰጡትን የማስታወቂያ አገልግሎት በውል ያስተላልፋል፤

8/ የተገነቡ መጠለያዎችን እና ተርሚናሎችን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ይረከባል፤

9/ በተርሚናሎችና በመጠለያዎች ላይ የጥገና ፍላጎት መረጃ ይሰበስባል፤

10/ ለተርሚናሎችና ለመጠለያዎች ጽዳት፣ ግንባታ፣ ጥገና እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች ለማከናወን የሚያስችል በጀት ያስይዛል፤

11/ ለመጠለያዎች ጽዳት እና ጥገና በቅጥር ወይም በውል ለሶስተኛ ወገን ያስተላልፋል፤

12/ ለተርሚናሎች ጽዳት፣ ጥገና፣ ጥበቃ፣ የካፍቴሪያ እና ስርዓት ማስከበር አገልግሎትን በውል ያስተላልፋል፤

13/ በስራ መዘርዝር ወይም በሚፈራረመው የስራ ውል መሰረት ስራውን የሚያከናውነውን አካል ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል ክፍተቶችን ያርማል፣ በበላይነት ይመራል፣ ይደግፋል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

14/ጉዳት የደረሰባቸውን መሰረተ ልማቶች የዋጋ ግምት ያዘጋጃል፤

15/ በመሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን በተመለከተ ከሚመለከታው አካላት ጋር በመሆን ጉዳት አድራሹ በህግ እንዲጠየቅ ያደርጋል፤

16/ በተርሚናሎች ውስጥ የማስታወቂያ ስራ ለመስራት በግልም ሆነ በድርጅት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፤

17/በመንግስት እና በግል አልሚ አካላት ለሚቀርቡ የመጠለያ እንዲሁም እንደ ተርሚናል አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን ይነሳልን ጥያቄዎችን ይቀበላል፣ ተገቢነቱን ይመረምራል፣ ምላሽ ይሰጣል፤

18/ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የጋራ ስምምነት ያዘጋጃል፣ ይፈራረማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

19/ እንደ ተርሚናል አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን በህግ ለተደራጁ ስርዓትና ደንብ የሚያስከብሩ ማህበራት በውል ያስተላልፋል፤

20/ ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አካላትና ለተጠቃሚዎች በመሰረተ ልማቶች አጠቃቀም ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

21/በተርሚናል ውስጥ የሚፈጠሩ የጥቅም ግጭቶችን እንዲፈቱ ይሰራል፡፡

## 11.ስለትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች አገልግሎት ቁጥጥር እና አጠባበቅ

1/ የህዝብና የጭነት መሰረተ ልማቶችን ደህንነት እና ንፅህና በቅጥር፣ ሶስተኛ ወገንን በማሳተፍ በኮንትራት ወይም ማህበራት እንዲደራጁ በማድረግ አማራጮችን በመጠቀም ያሰራል፣

2/ ለመሰረተ ልማት ቁጥጥርና አገልግሎት አጠባበቅ የሚረዱ የትምህርት ዝግጅት፣የስራ ልምድ፣ የስራ ሰዓት፣ የሰው ኃይል ብዛት መስፈርቶችን በማዘጋጀት ይተገብራል፤ በዚሁ መሰረት፡-

ሀ) የመጠለያ ፅዳትና ደህንነት የስራ ሰዓት ከጠዋቱ 12፡30 እስከ ቀኑ 6፡00 ሆኖ ተሳፋሪዎችን ደህነታቸው እንዲጠበቅ የጽዳት ስራው ከ12፡30 እስከ 1፡30 ባለው ውስጥ መሆን ይኖርበታል፤

ለ) አንድ የመጠለያ ፅዳት የሚያከናውን ሰራተኛ ቢያንስ 2 መጠለያዎችን ማፅዳት አለበት፤

3/ በመሰረተ ልማት አገልግሎት ቁጥጥር እና አጠባበቅ ሊውል የሚችል ከስራው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ወርሃዊ ክፍያ ይተምናል፣ ክፍያ በመፈፀም ያሰራል፤

4/ የሰራተኞችን የዕለት የሰዓት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ በቅ/ጽቤት አማካኝነት እንዲያዝ ያደርጋል፣

5/ አስፈላጊውን የመሰረተ ልማት ደህንነት የድጋፍና የክትትል ስራዎች ያከናውናሉ፣

6/ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው አካላት በጨረታ ይሰጣል፣

7/ የስራ ውል ያዘጋጃል፣ ይፈራረማል፣

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 12. <u>የመጠለያ እና የተርሚናል የይነሳልኝ ጥያቄ አቅራቢዎች የአፈታት ሂደት</u>

1/ የመሰረተ ልማት ይነሳልኝ ጥያቄ አቅራቢ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟላ ይገባል፡-

ሀ) በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ ያለው፣

ለ) ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የግንባታ፣ የግንባታ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ህጋዊ ፍቃድ ያለው፣

ሐ) መጠለያው የተገነባበት የይዞታውን ስፋት 50% እና ከዚያ በላይ የሚሸፍን ከሆነ፣

መ) የይነሳልኝ ጥያቄ አቅራቢውን ይዞታ መግቢያ መውጫ የሚሸፍን ከሆነ፣

2/ ጥያቄ አቅራቢው ይነሳልኝ ያለበትን ምክንያት ለትራንስፖርር ቢሮ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በፅሁፍ ያቀርባል፤

3/ ጥያቄ የቀረበለት የትራንስፖርት ቢሮ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የጥያቄውን አግባብነት በ7 ቀናት ውስጥ መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ አመራር ያቀርባል፤

4/ የትራንስፖርር ቢሮ የበላይ አመራርም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ በ7 ቀናት ውስጥ ይሰጣል፤

5/ መሰረተ ልማቱ እንዲነሳ የተወሰነለት አካል ከማንሳቱ ጋር የተያያዘውን ወጭ እና መልሶ መትከል ራሱ የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

6/ የማንሳትና መልሶ የመገንባት ስራ የሚከናወነው ደረጃውን በጠበቀ የስራ ተቋራጭ ሲሆን ስራው ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ቅ/ጽ/ቤት በሚመድበው ባለሙያ ክትትል ይደረግበታል፤

7/ ጥያቄ አቅራቢው የመጠለያውን ማስነሻ ዋጋ በትራንስፖርት ቢሮ የባንክ አካውንት ገቢ ማድረጉን የሚያሳይ ህጋዊ ማረጋገጫ ለቢሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤

8/ ጥያቄ አቅራቢው አካል በራስ አቅም የሚያስነሳ ከሆነ የሚነሳው ንብረት ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በሚመድበው ባለሙያ ክትትል አማካይነት እንዲነሳ ይደረጋል፤

9/ ጥያቄ አቅራቢው የትራንስፖርር ቢሮ ባለሙያ በተገኘበት ብቻ ማንሳት የሚችል ሆኖ በንብረቱ ላይ ጉዳት ከገረሰ የደረሰውን የንብረት ካሳ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

## 13. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

1/ ተርሚናሎችንም ሆነ መጠለያዎችን ከተገነቡበት አገልግሎት ውጪ ለሌላ ተግባር መጠቀም፤

2/ በመጠለያዎችና በተርሚናሎች የሚተላለፉ የማስታወቂያ መልዕክቶች የህዝብን ሞራል እና እሴት የሚጋፉ እንዲሁም ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው መሆን የለባቸውም፤

3/ ከትራንስፖርር ቢሮ እውቅና ውጪ በመጠለያዎች አካል ላይ ማንኛውንም ማስታወቂያ መለጠፍ፤

4/ በጭነት ተርሚናል ውስጥ ከተፈቀደው የጭነት ልክ በላይ መጫን፤

5/ በተርሚናል ውስጥ የተርሚናሉን የህዝብና የተርሚናሉን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ የሚቀጣጠሉና የሚፈነዱ ጭነቶችን መጫን፤

6/ በተርሚናሎች ውስጥ ከተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች ውጪ አገልግሎት መስጠትም ሆነ ማቆም፤

7/ ከብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች ውጪ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን 15 ሜትር ርቀት ባነሰ ቦታ ላይ ማቆም፤

8/ በተርሚናሎች እና በመጠለያዎች አቅራቢያ የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ክፍት አድርጎ መተው፤

9/ በጭነት ተርሚናሎች ውስጥ የተራገፉ ጭነቶች ከአንድ ቀን ወይም ከ24 ሰዓት በላይ ማስቀመጥ፤

10/ በተርሚናሎች ውስጥ ከትራንስፖርር ቢሮ እውቅና ውጪ እንዲሁም የደንብ ልብስና የደረት መታወቂያ ባጅ ሳያደርጉ የተራ ማስከበር፤

11/በውል ከተፈቀደው የማስታወቂያ አገልግሎት የጊዜ ገደብ ውጪ ማስታወቂያዎችን ማቆየት፤

12/ በአንድ የመንገድ መስመር ላይ እንደ ተርሚናል ለአገልግሎት መስጠት፤

13/ በመጠለያው አካል ላይ መቀመጥ፣ በመጠለያው ወንበር ላይ ምንም ዓይነት ዕቃዎችን ማስቀመጥ እንዲሁም ለቆሻሻ መጣያነት ከተቀመጡ ቅርጫቶች ውጪ ማንኛውንም ቆሻሻ መጣል፤

14/ የመጠለያዎችና የተርሚናሎች የጽዳት አጠባበቅ የጊዜ ሁኔታ ደህንነትና ምቾት የሚጋፋ፤

15/ ማንኛውም የብዙሃን ትራንስፖርት አገልገሎት ሰጪ አካል ከመጠለያዎች ወይም ከፌርማታዎች ውጪ ተሳፋሪዎችን መጫንና ማውረድ፤

16/ በመጠለያ ዙሪያ ባሉ ቦታዎች ግንባታ አድራጊ አካል የግንባታ ቦታውን ሳይከልል መስራት እንዲሁም የግንባታ ተረፈ ምርቶችን ማከማቸት፤

17/ በመጠለያዎቹ ውስጥ ጫት መቃም፣ አልኮል መጠጥ መጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስና ሌሎች የተከለከሉ አደንዛዥና አነቃቂ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም፡፡

14.<u>ቅድሚያ ስለመስጠት</u>

ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በመጠለያው የሚጠቀሙ ሕጻናትን፣ ነፍሰጡር እናቶችን፣ አረጋውያንን፣ አቅመ ደካሞችንና አካል ጉዳተኞችን ቅድሚያ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

15.<u>ስለተጠያቂነት</u>

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

16.<u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉትን ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

17.<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ቢሮው ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

18.<u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ከሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳዊት የሺጥላ

የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ